★ዴሞክራሲያ★

" የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ፓርቲ ልሣን"

ቅጽ 50፣ ቁ. 3 መስከረም 2015 ዓ. ም


# የህወሓት/ተሓህት/ወያኔ ምንነት

የአገራችን ኢትዮጵያ ህልውና በጥያቄ ውስጥ ሲገባ ይህ የመጀመሪያ ጊዜ አይደለም፡፡ የአሁኑን ለየት የሚያደርገው ግን የሕዝባችንንና የአገራችንን ታሪክ ፈጽሞ የካደ፣ ከውስጥ የበቀለ፣ ከውጭ ታሪካዊ ጠላት ጋር ያበረ የእናት ጡት ነካሽ የሆነው አሸባሪው ህዝባዊ ወያነ ሓርነት ትግራይ (ህወሓት) በሚባል ድርጅት የሚመራ መሆኑ ነው፡፡

የውጭ ጠላቶች፣ እንደ ግብጽ፣ ቱርክ፣ ጣሊያን ዓይነቶቹ ሲመጡ፣ ከቆዳ ቀለም አንስቶ፣ በቋንቋና ባህል ከሕዝባችን ፈጽሞ የተለየ ስለሆነ የውጭ ወራሪ መጣብህ በማለት ሕዝቡ እንዲከላከል ጥሪ ማድረግ ቀላል ነው፡፡ እንዲህም ስለሆነ ነው በአፄ ዮሃንስ ዘመን ግብጾች፣ ቱርኮች እንዲሁም ጣሊያኖች ኢትዮጵያን ለመውረር በቀይ ባሕር በኩል ሲመጡ፣ በጀግናው ራስ አሉላ አባ ነጋ ወታደራዊ አመራር አሸንፈን የአገራችንን የግዛት አንድነትና ሉዓላዊነት እንዲሁም የሕዝባችንን አንድነት አስከብረን በውጭ ኃይሎች ያልተገዛች አገር አድርገን አገራችንን በክብር ማቆየት የቻልነው፡፡

ህወሓት/ወያኔ የሚባል የአሁኑ ጠላት የአገራችንን ታሪክ ከሃቅ የራቀ መልክ አስይዞ፣ ለበርካታ ሺህ ዓመታት ተጋብቶና ተዋልዶ፣ የአገሩን አንድነትም ለማስጠበቅ በጋራ ደሙን አፍስሶ፣ አጥንቱን ከስክሶ የኖረን ሕዝብ እንዲሁም አድዋ ላይ የፋሽሽት ጣሊያንን ወረራ በአንድነት ድባቅ በመምታታ ለጥቁር ሕዝቦች ሁሉ ኩራት የሆነውን ሕዝባችንን በዘር በመለያየት እርስ በርስ እያጋደለ፣ አሁን ያለንበት ደረጃ በማድረስ የአገራችንን የግዛት አንድነትና ሉዓላዊነት አደገኛ ሁኔታ ላይ በማድረስ መበታተን ደረጃ ላይ አድርሷታል፡፡

ለዚህ አደገኛ ሁኔታ መፍትሄ ለመሻት ምን ማድረግ ይኖርብናል? ብለን ስንጠይቅ መንስዔው ምን እንደሆነ እንድናይ እንገደዳለን፡፡ የትም እንሂድ የት ምንጩ ይህ ህወሓት/ወያኔ የሚባል እኩይ ድርጅት እንደሆነ እንገነዘባለን፡፡ ይህ ድርጅት በታሪኩና በኢትዮጵያዊነቱ ኩሩ ከሆነው የትግራይ ሕዝብ ጋር ምንም እንኳን ትግራይ የሚለውን የኩሩውን ሕዝብ ስም በስሙ ላይ የለጠፈ ቢሆንም አንድ እንዳልሆነ ለሁሉም ግልጽ ሊሆን ይገባል፡፡ የህወሓት መሪዎች ለትግራይ ሕዝብ ደንታ ስለሌላቸው ሮጠው ያልጠገቡ ሕፃናትን በጦርነቱ በመማገድ ወላጆችንና አዛውንቶችን ያለልጅ ማስቀረታቸው ህወሓት የትግራይ ሕዝብ ጠላት መሆኑን በግልጽ ያመለክታል፡፡

ህወሓት/ወያኔ በተለያዩ መንገዶች በመጠቀምና ተግባራዊ በማድረግ አገራችን የተወሳሰቡ ችግሮች ውስጥ እንድዘፈቅ አድርጓታል፡፡ ለምሳሌ፡-

1. ከክርስቶስ ልደት በፊት ጀምሮ፣ በታሪክ የተመዘገበውን የአገሪቱንና የሕዝቧን አንድነት በመካድ፣ አንድነቱ ከ100 ዓመት አያልፍም በሚል ሕዝቡ እርሱ በርሱ እንዲዋጋ አድርጓል፡፡
2. የአክሱም ነገሥታት ክርስትናን በመቀበል ሕዝቦቿ ጥብቅ ሃይማኖታዊ ትስስር እንዲኖራቸው አድርጓል፡፡ የአክሱም ተወላጅ ቅዱስ ያሬድ ያስጀመረው የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን ዝማሬ እስከ አሁን ድረስ በመላ አገሪቷ እንደዳበረ በታሪክ ተዘግቧል፡፡ ህወሓት/ወያኔ ይህን አክሱም የፈለቀውን ታሪካዊ እድገት በመካድ በሕዝቦቿ መካከል መለያየትን በመፍጠር፣ አሁን ያለንበት የጦርነት ሁኔታ ውስጥ በማስገባት ሕዝባችንን በስቃይ እንዲኖር አድርጓል፡፡
3. በአገራችን ውስጥ የሚነገሩ ከስድስት በላይ ቋንቋዎች መሠረታቸው አክሱም ላይ የተጀመረው ግዕዝ ነው፡፡ ከግዕዝ በመነሳት የዳበሩት ቋንቋዎች፣ ኤርትራ ውስጥ የሚነገረው ትግረ፣ በኤርትራና ትግራይ የሚነገረው ትግርኛ፣ የአገራችን የመንግሥት የሥራ ቋንቋ የሆነውና በአብዛኛው የኢትዮጵያ ሕዝብ የሚነገረው አማርኛ፣ ጉራግኛ፣ አደርኛ፣ አርጎብኛ እንዲሁም ጥቂት የከሰሙ ቋንቋዎች ይገኛሉ፡፡ ይህንንም እድገትና ትስስር ህወሓት/ወያኔ ፈጽሞ በመካድ፣ ለሺህ ዓመታት በደምና በአጥንት፣ እንዲሁም በታሪክ የተጋመደውን ሕዝባችንን ምንም ግንኙነት እንደሌለው በማድረግ አሁን በምንገኝበት አስጊ ሁኔታ ላይ አድርሶናል፡፡

ኢትዮጵያን የመበታተን እኩይ ዓላማው አገራችን በቅኝ ለመግዛት መጥተው በጀግኖች አባቶቻችንና እናቶቻችን ድባቅ ተመትተውና የተመለሱ ጠላቶቻችን ያቀዱልንን ነው ህወሓት/ ወያኔ በተግባር ለማዋል የታገለው፡፡ የኢትዮጵያ ሕዝብ በታሪኩ ውስጥ በርካታ ጀግኖችና የጦር መሪዎች አፍርቷል፡፡ አፄ ዮሐንስ የአገራችውን የግዛት አንድነትና ሉዓላዊነት ለማስከበር ሕዝባቸውን አሰልፈው በሱዳን በኩል ከመጣው ወራሪ ጋር ሲፋለሙ ሕይወታቸው ቢያልፍም ደርቡሹን አሸንፈው በመጣበት እግሩ እንዲመለስ አድርገዋል፡፡ በሰሜን አገራችንን ለመውረር በርከት ያሉ ሙከራዎች ያደረጉት ግብጽ፣ ቱርክና ጣሊያንን በማሳፈር ኤርትራ ውስጥ የኢትዮጵያን ጦር የመሩትና በተለያየ ጊዜ አይቀጡ ቅጣት እየቀጡ የመለሱት የተንቤኑን ራስ አሉላ አባ ነጋንም እናገኛለን፡፡ ጣሊያን አገራችንን እንደገና ለመውረር ሲትሞክር ዓድዋ ላይ በተደረገው ውጊያ ሕዝባቸውን አሰልፈው ጠላት እንዲሸነፍ ካደርጉት የጦር አዝማቾች አንዱ አሁንም ራስ አሉላ አባነጋ ናቸው፡፡ ጣሊያን በሁለተኛው የዓለም ጦርነት አገራችንን ለመውረር በመጣችበት ወቅት የአምስት ዓመት አርበኝነት ከመሩት ውስጥ ራስ ስዩም መንገሻ (የአፄ ዮሃንስ የልጅ ልጅ)ና ራስ አሉላ አባነጋ ይገኙበታል፡፡

**ጎጠኛና አረመኔ የሆነውና** እስከ ቅርብ ጊዜ **በሥልጣን ላይ የነበረው ህወሓት/ወያኔ በምንም መልኩ ቀደም ሲል ራሱን ወያኔ (ቀዳማይ ወያኔ ይሉታል) ብሎ ከሰየመው የሽኩቻ እንቅስቃሴ ጋር የሚያገናኘው ነገር እንደሌለ እንዲታወቅ ያስፈልጋል፡፡** በ1933 **ዓ.ም ፋሽሽት ጣሊያን በጀግኖች አባቶቻችንና እናቶቻችን ቆራጥ ተጋድሎ ድል ተመትታ ካገር ስትወጣ የአፄ ኃይለሥላሴ መንግሥት በትረ መንግሥቱን እንደገና ይቆጣጠራል፡፡ የአፄው መንግሥት ያልተደላደለ ስለነበርና የመንግሥት አውታሩም በመላው የአገሪቷ ክፍሎች ውስጥ በሚገባ ስላልተዘረጋ ሽፍትነት በጣም አስቸግሮ ነበር። በትግራይ ክፍለሃገር፣ ዋጅራት በሚባል ቦታ በሽፍቶች የተማረረው ሕዝብ ተሰብስቦ ራሱን ለመከላከል ይማማላል። ምክክሩንም "ገረብና ንሓልው" በሚል ይሰይመዋል። ገረብና ንሓልው ቃል በቃል ሲተረጎም ወንዛችንን እንጠብቅ ማለት ነው፡፡ ባህላዊ አባባሉ**

ግን አካባቢያችንን ከሽፍቶች እንጠብቅ ማለት ነው። ባላገሩ ይህን ወስኖ፣ አልቢን፣ ምንሽሩን፣ጎራዴውን ታጥቆ፣ በመንግሥት ላይ ግን ሳያምጽ አካባቢውን ቢጠብቅም፣ በመንግሥት ዓይን ግን ያለፍቃድ መንግሥታዊ ሥልጣን መውሰድ ተደርጎ ስለታየ የአፄው መንግሥት አልተደሰተም። ይህን ጉዳይ "መልክ" ለማስያዝም፣ በእንግሊዞች እርዳታ ለመጀመሪያ ጊዜ በዘመናዊ መንገድ በመቋቋም ላይ የነበረውን ጦር ወደ ዋጅራት ይላካል፡፡ በዚህ የመንግሥት እርምጃ በመንግሥትና በሕዝቡ መካከል ቅራኔ ይፈጠራል። በራስ ስዩም መንገሻ ላይ ቅሬታ የነበራቸው የእንደርታ (መቀሌ ከተማ የሚገኝበት አውራጃ) ባላባታዊ ግለሰቦች፣ እነ ብላታ ኃይለማሪያም፣ የተፈጠረውን ቅራኔ በማራገብ በራስ ስዩም (የአፄ ዮሃንስ የልጅ ልጅ) ላይ ያምጻሉ። <u>ይህን ዓመጽ ወያኔ ይሉታል</u>። ለአፄ ኃይለሥላሴ ግን በራስ ስዩም ላይ ማመጽ በራሳቸው ላይ ማመጽ ስለሆነባቸው ጦሩን ልከው በአማጺዎቹ ላይ ያዘምታሉ። ወያኔ የባላባቶች የእርስ በእርስ ሽኩቻ እንጂ የትግራይን ሕዝብ ከጭቆና ለማገላገል ወይም ትግራይን ከኢትዮጵያ ለመገንጠል የተደረገ እንቅስቃሴ እንዳልነበረ መገንዘብ ያስፈልጋል።

ህወሓት/ወያኔ የሚባለው ጎጠኛ ድርጅት ፈጽሞ ዴሞክራሲያዊ አይደለም፡፡ የፖለቲካ ድርጅት ዴሞክራሲያዊ ባህሪ መገለጫ አንዱ ለሌሎች የፖለቲካ ድርጅቶች የሚኖረው አመለካከት ነው፡፡ አንድ ዴሞክራሲያዊ ነኝ የሚል ድርጅት በአገሩ ውስጥ የሚገኙ የፖለቲካ ድርጅቶችን የመደራጀትና የመንቀሳቀስ መብታቸውን ማክበር ይጠበቅበታል፡፡ ህወሓት/ወይኔ ይህ ባህሪ ስላልነበረው ገና ከመነሻው በአካባቢው ከነበሩ ድርጅቶች ጋር የነበረውን ግንኙነት እንዴት ሊፈታ እንደሞከረ እንመልከት፡፡

1. **ከተጋድሎ ሓርነት ትግራይ (ተሓት) ጋር የነበረው ግንኙነት፡-**

   ተሓት ምንም እንኳን ልክ እንደ ወያኔ አማሮች ጠላቶቻችን ናቸው፣ ከኢትዮጵያ መገንጠል አለብን ብሎ ያምን የነበረ ድርጅት ቢሆንም፣ ህወሓት/ወያኔ ፍጹም አሻጥር በተሞላበት መንገድ፣ ዓላማችን አንድ ስለሆነ ለምን አንተባበርም በማለት ስብሰባዎችን በማካሄድ "ስምምነት" ላይ ይደረሳል፡፡ "ስለተዋሃዱ" ነገሩን እውነት ለማስመሰል ከብት ታርዶ እራት ተበልቶ አንድ ላይ እንደር በማለት ሌሊት በተኙበት፣ አንድ ከማምለጡ በስተቀር፣ አመራሩን በሙሉ አርደው ድርጅቱን ደመሰሱ፡፡ የትግራይ ተወላጆች በሆኑና በአቋም ደረጃም ልዩነት በሌላቸው ላይ ይህን ከፈጸሙ በሌሎች ላይ ምን ሊይደርጉ እንደሚችሉ መገመቱ አስቸጋሪ አይሆንም፡፡

2. **ከኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ኅብረት (ኢዴኅ) ጋር የነበረው ግንኙነት**

   ኢዴኅ በዚያን ወቅት እንደተቋቋሙ ሌሎች ድርጅቶች፣ ህወሓት/ወያኔን ጨምሮ፣ ፀረ ወታደራዊ አገዛዝ (ደርግ) ሆኖ የተመሠረተ ድርጅት ነበር፡፡ ፀረ ዴሞክራሲና ፀረ ዴሞክራሲያዊ ድርጅት የሆነው ህወሓት/ወያኔ ኢዴኅ ላይ ጦርነት ከፈተ፣ በሁለቱም ወገን የብዙ አባላት ሕይወት ተቀጠፈ፣ ኢድኅም እንዲበተን ሆነ፡፡

## 3. ከኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ፓርቲ (ኢሕአፓ) ጋር የነበረው ግንኙነት

ኢሕአፓና ህወሓት/ወያኔ ወደ ትግራይ የገቡት ደርግ የመሬት ላራሹ አዋጅ ባወጀ በአንድ ወይም ሁለት ወራት ልዩነት ሲሆን ኢሕአፓ በሰሜን ምሥራቅ ትግራይ ዓጋሜ አውራጃ፣ ልዩ ስሙ ዓሲምባ ሲገባ ወያኔ በደቡብ ምዕራብ ትግራይ ሽረ አውራጃ ልዩ ስሙ ደደቢት በሚባል ቦታ ገባ፡፡ በኢሕአፓ በኩል በነበረው ዴሞክራሲያዊ አመለካከት፣ ማንም ቡድን፣ የኢትዮጵያን የግዛት አንድነትና ሉዓላዊነትን እስካልተጻረረ ድረስ የመደራጀት መብቱን ማክበር ነው፡፡ ከዚያም አልፎ በዚያን ወቅት በሥልጣን ላይ ከነበረው ፀረ ዴሞክራሲና ፋሽሽታዊ ደርግ ጋር እስካልተባበረ ድረስ ከሌሎች ኢትዮጵያ ውስጥ ከነበሩ ኃይሎች ጋር ለመተባበር ዝግጁ ነበር፡፡ ኢሕአፓ በጋራ መሥራትን በሚያስተጋባበት ወቅት የህወሓትን ምንነት በሚገባ አልተረዳም ነበር፡፡ ይህን የኢሕአፓ አቋም ለህወሓት/ወያኔ በተደጋጋሚ በመግለጽ አብሮ ለመታገል ውይይት በሚደረግበት ወቅት ነበር አዘናግቶና በክህደት ከትግራይ ክፍለሀገር ውጡ በማለት ኢሕአፓን የወጋው፡፡

## 4. ከኦሮሞ ነፃነት ግንባር (ኦነግ) ጋር የነበረው ግንኙነት

የህወሓት/ወያኔ ቡድን የሚፈልገውን ነገር ያሳካልኛል ብሎ ካሰበ ዓይን ያወጣ ውሸት ከመዋሸት ወደኋላ ብሎ አያውቅም፡፡ ከኦሮሞ ነፃነት ግንባር ጋር፣ ደርግ ሥልጣን ላይ በነበርበት ወቅት፣ የህወሓት/ወያኔን ባህሪ እስካልተፃረረ ድረስ፣ እየተደጋገፉ፣ ጓዴ፣ ጓዴ እየተባባሉ አዲስ አበባ እስኪገቡ አብረው ሠርተዋል፡፡ የኢትዮጵያን ሕገ መንግሥትንም በጋራ በመፃፍና የአዲስ አበባው ጉባዔ ላይም እነሱን የማይመስሉ ቡድኖችን እስከማግለል ድረስ ተባብረዋል፣ የመንግሥትን ሥልጣንንም አብረው ያዙ፡፡ ተመሳሳይ አመለካከትና ባህሪም ስላላቸው፣ ሥልጣን ከያዙ በኋላ ጠላት ብለው በፈረጁት የአማራ ሕዝብ ላይ አረመኔያዊ ግድያና ጭፍጨፋ አካሂደዋል፡፡ ብዙም ሳይቆዩ የመጀመሪያውን "አገር አቀፍ" ምርጫ ለማካሄድ ሲዘጋጁ ህወሓት/ወያኔ የኦነግን ጦር ከቦ ሠራዊቱን በተነው፣ ድርጅቱን እንዳልሆነ አረገው ከሥልጣንም አባረረው፡፡

## 5. ከኤርትራ ግንባሮች ጋር የነበረው ግንኙነት

ህወሓት/ወያኔ ከመጀመሪያ ወዳጁ፣ ተጋድሎ ሓርነት ኤርትራ (ጀብሃ) ጋር እስከ 1968 ዓ ም ድረስ ጥሩ ትብብር ያደርግ ነበር፡፡ ከዚያ በኋላ ግን ግንኙነታቸው በሙሉ ከህዝባዊ ሓይልታት ኤርትራ (ሻዕቢያ) ጋር ሆነ፡፡ ከጀብሃ ጋር የነበረው ግንኙነት ፈጽሞ ተቋረጠ፡፡ በ1973 ዓ ም ሻዕቢያና ህወሓት/ወያኔ ግንባር ፈጥረው ጅብሃን ደመሰሱ፡፡ የሁለቱ ድርጅቶች ግንኙነት መተከላዊ ስላልነበረ ሐምሌ 1973 ዓ ም ሻዕቢያና ወያኔ ጾረና አካባቢ ተዋጉ ሆኖም እንደምንም ታረቁ፡፡ በ1998 ዓ ም በሻዕቢያና ህወሓት/ወያኔ መካከል የባድመው ጦርነት ከ 70,000 እስከ 100,000 የሚሆን የዜጎችን ሕይወት ከቀጠፈ በኋላ ጦርነቱ የተጠናቀቀ ቢሆንም ሰላም የተፈጠረው ግን ህወሓት/ወያኔ ከሥልጣን ወርዶ ዶ/ር አብይ አህመድ መጋቢት 24 2010 ዓ. ም. ጠቅላይ ሚኒስቴር ከሆኑ በኋላ ነው፡፡

ከላይ እንደተመለከተው ህወሓት/ወያኔ በምንም ዓይነት መልኩ ዴሞክራሲያዊ ስላልሆነ፣ ለሕዝብ ምንም ደንታ ስለሌለው፣ ሁሌ እኔ ብቻ በሥልጣን ላይ ካልሆንኩ የሚል ፅኑ እምነት ስላለው፣ የአፅላፍ ሕዝብ መሞትና፣ መሰደድን ዋናው ምክንያት ስለሆነ፣ በርካታ እናቶች እህቶችን አስገድዶ የደፈረ (የ80 ዓመት መነኩሴን ጨምሮ) ስለሆነ፣ በቁጥር ማስፈር የሚያስቸግር የሕዝብ ንብረትና የአገር ልማታዊ ተቋማትን ስላወደመ፣ የሕዝብ አንድነትንና ወንድማማችነትን/እህትማማችነትን ለመበተን

ያለማቋረጥ ስለሠራ፣ የአገሪቱን የግዛት አንድነትና ሉዓላዊነትን አስጊ ሁኔታ ላይ ስላደረሰ.....ወ.ዘ.ተ የሚታመን ድርጅት አይደለም፡፡ የአገር አጥፊዎች፣ የግለኞች፣ የአምባገነኖች፣ የአሸባሪዎች፣ የአረመኔዎች....ወ.ዘ.ተ ቡድን ነው፡፡ ህወሓት/ወያኔ የትግራይ "ነፃ አውጭ ነኝ " በማለት በስለላና በወታደራዊ ኃይል ረግጦ የሚገዛ ድርጅት እንጂ ዴሞክራሲን ለሕዝብ ወይም ለአባላቱ የሚሰጥ አይደለም፡፡ የትግራይ ሕዝብ ታፍኖና ተረግጦ በዚህ አሻባሪ ድርጅት የጭለማ ዘመን እየኖረ መሆኑን እናውቃለን፣ መላው የኢትዮጵያ ሕዝብ፣ በሚገባ የሚያውቀው ሃቅ ነው፡፡

ስለዚህ ለወያኔ ደንታ የማይሰጡትን ጉዳዮች እውን ለማድረግ፣ በድርድር የሚባለው ነገር በፍጹም አይሠራም፡፡ ድርድር በመርኅ ደረጃ የችግር መፍቻ መንገድ ነው፡፡ አገራችን አሁን ካለችበት ችግር ማውጣት የሚቻለው፣ ጥምር ጦሩ አሁን እየተደረገ እንዳለው እስከ መጨረሻ በመሄድ ይህን አረመኔ ቡድን በጉልበት ማንበርከክና ጨርሶ መደምሰስ ነው፡፡ ህወሓት/ወያኔ ገና ጫካ በነበረበት ጊዜ የደርግን መንግሥት እንደራደር ዝግጁ ነኝ እያለ ደርግ አንዴ ጣሊያን አገር በሌላ ጊዜ ናይሮቢ ተደራዳሪ ሲልክ አሸባሪው ወያኔ ብዙ ከተሞችን በጦርነት ደመሰሰ፡፡ ህወሓት/ወያኔ ድርድር የሚለው የሚቸነፍ ሲመስለው ለጊዜ መግዣ እንጂ ከልቡ ሰላም የሚፈልግ ድርጅት ስለሆነ አይደለም፡፡

የኢትዮጵያ መንግሥት ከአሁን ቀደም እንዳደረገው "ሰላም ለማምጣት" ማፈግፈግ ጨርሶ አልሠራም፡፡ መንግሥት ይህን ባደረገ ቁጥር፣ ውጤቱ ህወሓት/ወያኔ ጊዜ እየገዛ፣ መልሶ እየተደራጀና ከሞቱ እያገገመ ሕዝባችንን ማሰቃየት፣ የአገራችንን የግዛት አንድነትና ሉዓላዊነት አሁን ካለችበት አፋፍ ገፍቶ ልትወጣ የማትችልበት ችግር ላይ ማድረስ ብቻ ነው፡፡

ከመንግሥት ዋነኛ ተግባሮቹና ግዴታው የአገሪቱን የግዛት አንድነትና የሕዝቡን በሰላም የመኖር መብቱን ማረጋገጥ ነው፡፡ ህወሓት/ወያኔ፣ ሸኔና ሌሎች ተመሳሳይ ቡድኖች እስካሉ ድረስ ሕዝቡ በሰላም ሊኖር አይችልም፡፡ መንግሥት እኒህ ዓይነት ቡድኖች እስካሉ ድረስ አገሪቱ አንድነቷ ተከብሮ ልትኖር እንደማትችል፣ ሕዝቧም በፈቀደው የአገሪቱ ክልል በሰላም ሊኖር እንደማይችል ማመን ይኖርበታል፡፡

ስለዚህ ኢትዮጵያውያንና ለኢትዮጵያ የቆመ ኃይል ሁሉ፣ በሥልጣን ላይ ያለው መንግሥትንም ጨምሮ፣ ይህን ፀረ ሕዝብ እኩይ ድርጅት እስከነተባባሪዎቹ የመጨረሻ ወሳኝ እርምጃ በመውሰድ አሁን አገራችን የምትገኝበትን አደገኛ ሁኔታ ለመቀልበስ ቆራጥ እርምጃ መውሰድ ይገባል፡፡

የኢትዮጵያ ሕዝብ ያለጥርጥር ያቸንፋል!